# ትምህርት 63

1. ሕዝቡ ሕፃናትን ወደ ኢየሱስ ስላመጡ ደቀመዛሙርቱ የገሰጹአቸው ለምንድን ነው?
ሀ- ደቀመዛሙርቱ ኢየሱስ በሕፃናት መቸገር የለበትም ብለው ስለ አሰቡ።

2. ኢየሱስ ሁሉንም ሕፃናት ይወዳል?
ሀ- አዎን።

3. ሕፃናት ከኃጢአት ከሞትና ከሰይጣን ባርነት መዳን ያስፈልጋቸዋል?
ሀ- አዎን።

4. ኢየሱስ «የእግዚአብሔርን መንግስት እንደ ሕፃን የማይቀበላት ሁሉ ከቶ አይገባባትም» ሲል ምን ማለቱ ነው?
ሀ- ኢየሱስ እኛ እንደ ሕፃን ልጅ በሆነ እምነት በእግዚአብሔር ካላመንን አንድንም ማለቱ ነው።

5. የሕፃን ልጅ እምነት ምን ይመስላል?
ሀ- የሕፃን ልጅ እምነት ሙሉ በሙሉ የተሟላ እምነት ነው።
ለ- የሕፃን ልጅ እምነት ከሙሉ ልብ የሆነ እምነት ነው።

6. ሀብታሙ ወጣት ኢየሱስን ምን ብሎ ጠየቀው?
ሀ- «የዘላለምን ሕይወት ለማግኘት ምን ላድርግ?»

7. የኢየሱስ መልስ ምን ነበር?
ሀ- ኢየሱስም «ለምን ቸር ትለኛለህ? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በስተቀር ቸር የለም» አለ።

8. ኢየሱስ እርሱ ቸር መሆኑን መካዱ ነበር?
ሀ-አይደለም።

9. ኢየሱስ እርሱ አምላክ መሆኑን መካዱ ነበር?

ሀ-አይደለም።

10. ታዲያ ኢየሱስ እንዲህ ያለው ለምን ነበር?
ሀ- ኢየሱስ እንዲህ ያለው ሰዎች ሁሉ በኃጢአት ስለተወለዱ ቸሮች ሊሆኑ እንደማይችሉ ሀብታሙ ሰው እንዲረዳ ስለፈልገ ነው።
ለ- በተጨማሪም ኢየሱስ እንዲህ ያለው ከኃጢአት ነፃ የሆነው እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ መልካም እግዚኣብሔር ብቻ መሆኑን ሀብታሙ ሰው እንዲረዳ ስለ ፈለገ ነው።

11. ሀብታሙ ሰው የዘላለም ሕይወት ማግኘት የሚቻለው እንዴት ነው ብሎ አሰበ?
ሀ- መልካም ሥራ በመስራት።

12. ሀብታሙ ወጣት ያልተረዳው ነገር ምን ነበር?
ሀ- ሀብታሙ ወጣት ያልተረዳው በውጭ የምንሰራቸው መልካም ስራዎች በውስጥ ያለውን ክፉ ልባችንን ሊለውጡት አለመቻላቸውን ነበር።

13. ሀብታሙ ሰው እያዘነ የሄደው ለምን ነበር?
ሀ- እጅግ ብዙ የሆነውን ሃብቱን ለመስጠት ፈቃደኛ ስላልነበረ።
ለ- ኢየሱስ ክፉ ልቡን እንዲለውጠው ፈቃደኛ ስላልነበረ።

14. ከክፉ ልባችን ሊያድነን የሚችለው ማን ብቻ ነው?
ሀ- ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው።

- ኢየሱስ የሰዎችን ልብ ስለሚያውቅ ሕዝቡን ስለስስት አስተማረ።

ሉቃስ 12:15

15- ደግሞም «የሰው ሕይወቱ በሀብቱ ብዛት የተመሰረተ ስላልሆነ ተጠንቀቁ፤ ከስግብግብነትም ሁሉ ራሳችሁን ጠብቁ» አላቸው።

- ሰዎች ለምን ይስገበገባሉ ?

- ምክንያቱም በኃጢአት ስለተወለዱ ነው።

- ምክንያቱም የሌላቸው ነገር እንዲኖራቸው ስለሚፈልጉ ነው።

- ብዙ ሰዎች ንብረትን በዚህ ዓለም ካሉ ነገሮች ሁሉ ይልቅ ይፈልጋሉ።
- ብዙ ሰዎች ንብረታቸውን ከእግዚአብሔር ይልቅ ይወዳሉ።

- ብዙ ሰዎች የሌሎች ሰዎችን ንብረት ያዩና ለራሳቸው ይፈልጉታል።

- ብዙ ሰዎች ብዙ ንብረት ቢኖራቸውና ሀብታሞች ቢሆኑ ደስተኞች እንደሚሆኑ ያስባሉ።

- ሰው በዚህ ዓለም ያለው ሀብት ሁሉ ቢኖረው ገሃነም እሳት ከገባ በኋላ ሀብቱ ሊረዳው ይችላል?

-አይችልም።

- ሕይወታችን የተትረፈረፈ ሀብት የግድ ያስፈልጉታል?
-አያስፈልጉትም።

- ንብረቶቻችን ከኃጢአት ከሞትና ከሰይጣን ሊያድኑን ይችላሉ?
- አይችሉም።

- ሰዎች እንዲረዱ ለማድረግ ኢየሱስ በምሳሌ ተናገረ።

ሉቃስ 12፥16-19

16-ቀጥሎም [ኢየሱስ] እንዲህ ሲል ምሳሌ ነገራቸው፤ «ዕርሻው እጅግ ፍሪያማ የሆነችለት አንድ ሀብታም ነበረ።

17-ይህም ሰው፥ ምርቴን የማከማችበት ስፍራ ስለሌለኝ ምን ላድርግ? ብሎ በልቡ አሰበ።

18-እንዲህም አለ፤ እንደዚህ አደርጋለሁ፤ ያሉኝን ጎተራዎች አፈርስና ሌሎች ሰፋ ያሉ ጎተራዎች እሰራለሁ፤ በዚያም ምርቴንና ንብረቴን አከማቻለሁ

19-ነፍሴንም፥ «ነፍሴ ሆይ ለብዙ ዘመን የሚበቃሽን ሀብት አከማችቼልሻለሁ፤ እንግዲህ ዕረፊ፤ ብዪ፤ ጠጪ፤ ደስም ይበልሽ» እላታለሁ።

-ኢየሱስ የሀብታሙን ገበሬ ምሳሌ ተናገረ።

- በአንድ ወቅት የሀብታሙ ገበሬ መሬት ብዙ ምርት ስላስገኘለት ገበሬው ምርቱን የሚያከማችበትን ስፍራ አጣ።

- ከዚያስ ሀብታሙ ገበሬ ምን ለማድረግ አስበ?

- ሀብታሙ ገበሬ ትልቅ ጎተራ ሊሰራና ምርቱን ሁሉ በዚያ ሊያከማች እንዲሁም ቀሪውን ዘመን ምንም ሳይሰራ በምቾት ሊኖር አሰበ።

- ሀብታሙ ገበሬ ብዙ ሀብት ስለ ነበረው ምንም ችግር እንደሌለበት አሰበ።

- ሀብታሙ ገበሬ ብዙ ሀብት ስለ ነበረው ሁሉ ነገር እንዳለው አሰበ።

- ሀብታሙ ገበሬ ብዙ ሀብት ስለነበረው እግዚአብሔርን በመርሳት እንደ ፈለገ ሆኖ ለመኖር አሰበ።

- ሀብታሙ ገበሬ እግዚአብሔርን ቢረሳውም እግዚአብሔር እርሱን ረስቶታል?

-አልረሳውም።

-ቀጥሎስ ኢየሱስ ሀብታሙ ገበሬ ላይ ምን ደረሰበት አለ?

ሉቃስ 12፡20

20- እግዚአብሔር ግን፥ «አንተ ሞኝ፤ ነፍስህን በዚህች ሌሊት ከአንተ ሊወስዱ ይፈልጓታል፤ እንግዲህ ለራስህ ያከማቸኸው ለማን ይሆናል?» አለው።

- ሀብታሙ ገበሬ ላይ ምን ደረሰበት?
- እግዚአብሔር እንዲሞት ጠራው።

- ሀብታሙ ገበሬ የሚሞትበትን ቀን የወሰነው ማን ነበር?
- እግዚአብሔር።

- ሰዎች ሁሉ የሚሞቱበትን ጊዜ የሚወስነው ማን ነው።
- እግዚአብሔር ብቻ።

- በሀብታሙ ገበሬ ትልቅ ሀብት ላይ ምን ደረሰበት?

- ሀብቱ ለሌላ ሰው ሆነ።

-እግዚአብሔር ሀብታሙን ገበሬ ሞኝ ብሎ የጠራው ለምን ነበር?

- ምክንያቱም ሀብታሙ ገበሬ እግዚአብሔርን በመርሳት እንደፈለገ ለመኖር ስላሰበ ነው።

- ሀብታሙ ገበሬን ብዙ የሆነ ሀብቱ አድኖታል?
- አላዳነውም።

- ሀብታሙ ገበሬ ሁሉም ነገር ነበረው?
- አልነበረውም።

- ሀብታሙ ገበሬ ብዙ ሀብት ነበረው ለርሱ ያልነበረው ምን ነበር?
- የዘላለም ህይወት።

- ኢየሱስ ምሳሌውን ተናግሮ ካበቃ በኋላ ምን አለ?

ሉቃስ 12፡21

21- ኢየሱስ እንዲህ አለ «ስለዚህ ለራሱ ሀብት የሚያከማች፤ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ዘንድ ሀብታም ያልሆነ ሰው መጨረሻው ይኸው ነው።»

- ኢየሱስ ለራሳችን ብዙ ሀብት ብናከማች በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ባለጠጎች ባንሆን የዘለዓለም ሞት እንደሚጠብቀን ተናገረ።

- ከብዙ ሀብት የሚበልጥ ምንድን ነው?

- በእግዚአብሔር ማመንና የዘላለም ሕይወት ማግኘት።

- ከዚያ ኢየሱስ አንድ ታሪክ ተናገረ።

ሉቃስ 16፡19-21

19- ደግሞም ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ «ሐምራዊና ቀጭን በፍታ የለበሰ፥ በየቀኑም በተድላ ደስታ የሚኖር አንድ ሀብታም ሰው ነበር።

20- በአንፃሩም መላ ሰውነቱ በቁስል የተወረረ አንድ አልዓዛር የሚባል ደኻ በዚህ ሀብታም ሰው ደጃፍ ይተኛ ነበር።

21- ከሀብታሙ ሰው ማእድ የወደቀውን ፍርፋሪ እንኳን ለመመገብ ይመኝ ነበር፤ ውሾችም እንኳን ሳይቀሩ መጥተው ቁስሉን ይልሱ ነበር።

- ይህ የሀብታሙ ሰውና የአልዓዛር ታርክ እውነተኛ ታሪክ መሆኑን በምን እናውቃለን?

-ምክንያቱም እነዚህ ሁለት ሰዎች በእርግጥ በምድር ላይ ስለነበሩ ነው።

- በታርኩ ውስጥ የተጠቀሱት ሁለት ሰዎች እነማን ነበሩ?

- አንደኛው ሀብታም ሰው ሲሆን ሌላኛው ደኻ ሰው ነበር።

- የደኻው ሰው ስም ማን ነበር?
- አልዓዛር።

- ይህ አልዓዛር የኢየሱስ ወዳጅና ከሞት ያስነሳው አልዓዛር አይደለም።

- ከሁለቱ ሰዎች የተባረከው ማን ነበር?

- የበፍታ ልብስ የለበሰውና የፈለገው ምግብ ሁሉ የነበረው ሀብታሙ ሰው ነበር?

- ሕመምተኛውና ምንም ምግብ ያልነበረው አልዓዛር ነበር?

- ምናልባት ሀብታሙ ሰው ነው ትሉ ይሆናል፤ ነገር ግን ታሪኩ ገና አላበቃም።

- ኢየሱስ በእነዚህ ሁለት ሰዎች ላይ ምን እንደ ተፈፀመ የተናገረውን አድምጡ።

ሉቃስ 16፡22

22-«ይህም ደኻ ሞተ፤ መላክእትም ወደ አብርሃም ዕቅፍ ወሰዱት። ሀብታሙም ሰው ድግሞ ሞቶ ተቀበረ።»

- ድኻው አልዓዛር ሲሞት ምን ተፈፀመ?

- መላአክት ተሸክመውት ወደ እግዚአብሔርና ወደ አብርሃም ወሰዱት።

- ሀብታሙ ሰው ምን ሆነ?
- ሀብታሙም ደግሞ ሞተ።

- የሀብታሙ ሰው ሀብት ከሞት ጠብቆታል?
- አልጠበቀውም።

-ሀብታሙ ሰው ከሞተ በኋላ ወዴት ሄደ?

ሉቃስ 16፥23

23-በሲኦልም እየተሰቃየ ሳለ ቀና ብሎ ከሩቅ አብርሃምን አየ፤ አልዓዛርን በዕቅፉ ይዞት አየ።

- ሀብታሙ ሰው ከሞተ በኋላ ወዴት ሄደ?
- ወደ ሲኦል፤ ዘላለማዊ ቅጣት ወደሚፈፀምበት ወደ ገሃም እሳት።

- ሰው በሚሞትበት ጊዜ መንፈሱ ወደየት ነው የሚሄደው ?

- ከእግዚአብሔር ጋር ለመሆን በቀጥታ ወደ መንግስተ ሰማይ ወይም የቅጣት ቦታ ወደ ሆነው ወደ ገሃም እሳት።

- አንዳንድ ሰዎች ሰው ሲሞት መንፈሱ በምድር ላይ ይንከራተታል ይላሉ።

- ይህ የሰይጣን ውሸት ነው።

- አንዳንድ ሰዎች ሰው ሲሞት መንፈሱ በሰማይና በምድር መካከል ወደሚገኘው የመቆያ ቦታ ይሄዳል ይላሉ።

- ይህም ደግሞ የሰይጣን ውሸት ነው።

- በመንግስተ ሰማይና በምድር መካከል የማቆያ ቦታ አለ?
- የለም።

- አንዳንድ ሰዎች የሞቱ አያቶቻቸውን ድምፅ መስማታቸውን ወይም ከሞተ ሰው መልዕክት መቀበላቸውን ይናገራሉ።

- ይህም ደግሞ የሰይጣን ውሸት ነው።

- ሰዎች የሚሰሟቸው ድምፆችና መልዕክቶች የሰይጣንና የአጋንንቱ ናቸው።

- ሰው ሲሞት መንፈሱ ከእግዚአብሔር ጋር ለመሆን በቀጥታ ወደ መንግስተ ሰማይ ወይም ወደ ሲዖል ነው የሚሄደው።

- አልዓዛር ሲሞት መንፈሱ ከእግዚአብሔር ጋር ለመሆን ወደ መንግስተ ሰማይ በቀጥታ ሄደ።

- ሀብታሙ ሰው ሲሞት መንፈሱ እሳትና የዘላለም ቅጣት ወደ ሞላበት ወደ ሲዖል በቀጥታ ወረደ።

-ሀብታሙ ሰው አብርሃምን አናገረው።

ሉቃስ 16፡24

24- እርሱም «አብርሃም አባት ሆይ ራራልኝ፤ በዚህ ነበልባል እየተሰቃየሁ ስለሆነ፥ አልዓዛር የጣቱን ጫፍ ውሃ ነክሮ ምላሴን እንዲያቀዘቅዝልኝ እባክህ ላክልኝ እያለ ጮኸ።»

- በመጀመሪያ ሀብታሙ ሰው አብርሃምን የጠየቀው ምን ነበር።

- አብርሃምን የጠየቀው አልዓዛር በጣቶቹ ጫፍ ውኃ ነክሮ ምላሱን እንዲያቀዘቅዝለት እንዲልክለት ነበር።

- ለምን?

- ሀብታሙ ሰው በእሳቱ ባህር ውስጥ እጅግ በጣም ይሰቃይ ስለ ነበር ነው።

- እግዚአብሔርን ለማመን የማይፈልጉ ሁሉ ከሞቱ በኋላ የሚሄዱት ወዴት ነው።

- ወደ ሲኦል ዘላለማዊ የቅጣት ስፍራ ወደ ሆነው ገሃም እሳት።

- እግዚአብሔር ኃጢአትን ይጠላል፤ ኃጢአትን በሞት ይቀጣል።

- አብርሃም ምን መለሰለት?

ሉቃስ 16፡25

25-አብርሃም ግን እንዲህ አለው፤ «ልጄ ሆይ፤ አንተ በምድራዊ ሕይወትህ ዘመን መልካም ነገሮችን እንደተቀበልህ፥ አልዓዛርም ደግሞ ክፉ ነገርን እንደተቀበለ አስታውስ፤ አሁን ግን እርሱ እዚህ ሲፅናና አንተ በስቃይ ላይ ትገኛለህ።”

- አብርሃም ምን መለሰለት?

- አብርሃም ሀብታሙ ሰው በምድር በነበረበት ጊዜ በምቾት ኖሮአል አሁን ግን መሰቃየት አለበት አለ።

- ደግሞም አብርሃም፣አልዓዛር በምድር በነበረበት ጊዜ ተሰቃይቶአል አሁን ግን ይፅናናል አለው።

- አልዓዛር ወደ መንግስተ ሰማይ የሄደው ደሃ ስለነበረ ነው?

- አይደለም

- አልዓዛር ወደ መንግስተ ሰማይ የሄደው ለምንድን ነው?
- በእግዚአብሔር ስላመነ?

- አልዓዛር በኃጢአት መወለዱን አውቋል።

- አልዓዛር እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁሉ በሞት እንደሚቀጣ አውቋል።

- አልዓዛር እግዚአብሔር እርሱን ለማዳን አዳኙን እንደሚልክ አምኗል።

- በእግዚአብሔር የሚያምኑ ሰዎች ሁሉ ሲሞቱ ወዴት ነው የሚሄዱት?

- ከእግዚአብሔር ጋር ለመኖር ወደ መንግስተ ሰማይ።

- ሀብታሙ ሰው ወደ ሲዖል የሄደው ሀብታም ስለሆነ ነው?
- አይደለም።

- ሀብታሙ ሰው ወደ ሲዖል የሄደው ለምንድን ነው?

- በእግዚአብሔር ማመን ስላልፈለገ ነው።

- ሀብታሙ ሰው በኃጢአት መወለዱን አላመነም።

- ሀብታሙ ሰው እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁሉ በሞት እንደሚቀጣ አላመነም።

- ሀብታሙ ሰው አዳኝ እንደሚያስፈልገው አላመነም።

- ሀብታሙ ሰው የኖረው ለትልቅ ሀብቱ ብቻ ነበር።

- አብርሃም ለሀብታሙ ሰው ሌላ ምን ተናገረ?

ሉቃስ 16፥26

26- ኢየሱስ እንዲህ አለ "ከሁሉም በላይ ከዚህ ወደ እናንተ ለማለፍ የሚፈልጉ እንደማይችሉ እዚያ ያሉትም ደግሞ ወደ እኛ እንዳይሻገሩ በእኛና በእናንተ መካከል ትልቅ ገደል ተደርጎአል።"

- አብርሃም በመንግስተ ሰማይና በስዖል መካከል ማንም ሰው መሻገር የማይችለው ትልቅ ገደል መኖሩን ተናገረ።

- ወደ ቅጣቱ ቦታ የገባው ሰው ማምለጥ ይችላል?
- አይችልም።

- አንድ ሰው ሞቶ ወደ ቅጣት ስፍራ ከገባ በኋላ መምለጫ መንገድ አይኖረውም።

- አንድ ሰው ሞቶ ወደ ቅጣት ስፍራ ከሄደ ከዘላለም እስከ ዘላለም በዚያ ይሆናል።

- የእግዚአብሔርን ቃል ለማድመጥ ካልፈለጋችሁ ወደ ቅጣት ቦታ ትሄዳላችሁ።

- የእግዚአብሔርን ቃል ለማድመጥ ካልፈለጋችሁ ከዘላለም እስከ ዘላለም በቅጣት ቦታ ትሆናላችሁ።

- ከዚያም ሀብታሙ ሰው አብርሃምን ሌላ ጥያቄ ጠየቀው።

ሉቃስ 16፡27-28

27- ሀብታሙ ሰው እንዲህ አለ፤ “አባት ሆይ፤ እንግዲያውስ አልዓዛርን ወደ አባቴ ቤት እንድትሰደው እለምንሃለሁ።
28- አምስት ወንድሞች ስላሉኝ፥ እነርሱ ወደዚህ የሥቃይ ስፍራ እንዳይመጡ ያስጠንቅቃቸው።”

- ሀብታሙ ሰው ለአብርሃም ያቀረበው ሁለተኛ ጥያቄ ምን ነበር?

- በእሳት ባሕርና በዘላለማዊ የቅጣት ቦታ እንዳይሠቃዩ አልዓዛር ሄዶ ወንድሞቹን እንዲያስጠነቅቃቸው አብርሃም እንዲልከው።

- ሀብታሙ ሰው በእሳት ባሕር ውስጥ እጅግ እየተሰቃየ ቢሆንም ወንድሞቹን ግን አስታውሶአል።

- በስዖል ሀብታሙ ሰው ምግብ ወይም ልብስ ጠይቋል?
- አልጠየቀም።

- በስዖል ሀብታሙ ሰው የዶሮ ወይም የፍየል ደም ጠይቋል?
- አልጠየቀም።

- ሰይጣንና አጋንንቱ ብዙ ሰዎችን አሳስተዋል።

- ብዙ ሰዎች የሞቱ ሰዎች ምግብ ወይም ብርድ ልብስ የዶሮ ወይም የፍየል ደም ያስፈልጋቸዋል ይላሉ።

- ይህ የሰይጣን ውሸት ነው።

- ሀብታሙ ሰው አልዓዛር ወደ ወንድሞቹ ሄዶ በእሳት ባሕርና በዘላለሙ ቅጣት እንዳይሠቃዩ እንዲያስጠነቅቃቸው ፈለገ።

- አብርሃም ለሀብታሙ ሰው ምን መለሰለት?

ሉቃስ 16፡29

29- አብርሃም ግን «ሙሴና ነቢያት አሉላቸው፤ እነርሱን ይስሙ» አለው።

- አብርሃም የሀብታሙ ሰው ወንድሞች ሙሴና ነቢያት አሉላቸው፤ እነርሱ ሙሴንና ነቢያትን መስማት አለባቸው አለው።

- አብርሃም ለሀብታሙ ሰው ወንድሞች ሙሴና ነቢያት አሉላቸው ሲል ምን ማለቱ ነው።

- አብርሃም ለሀብታሙ ሰው ወንድሞች በሙሴና በነቢያት የተፃፉት የእግዚአብሔር ቃል አሉላቸው ማለቱ ነው?

- አብርሃም የሀብታሙ ሰው ወንድሞች ማድረግ ያለባቸው ምንድን ነው አለ?

- "እነርሱ ማድረግ ያለባቸው የእግዚኣብሔርን ቃል ከመጽሐፍ ቅዱስ ማንበብና መስማት ነው" አለ።

- እኛ የእግዚአብሔርን ቃል ከሰማንና ካመንን ወደ ዘላለማዊው የቅጣት ቦታ አንሄድም።

- ሀብታሙ ሰው ምን መለሰለት?

ሉቃስ 16፡30

30-እርሱም « አብርሃም አባት ሆይ፤ እንደዚህ አይደለም፤ አንድ ሰው ከሙታን ተነሥቶ ቢሄድላቸው ንሰሓ ይገባሉ» አለ።

- ሀብታሙ ሰው "አንድ ሰው ከሙታን ተነሥቶ ወንድሞቹን ቢያስጠነቅቃቸው ንሰሓ ይገባሉ" አለ።

- አብርሃምስ ምን መለሰለት?

ሉቃስ 16፡31

31-«አብርሃምም፥ "ሙሴንና ነቢያትን የማይሰሙ ከሆነ፥ አንድ ሰው ከሙታን ቢነሳ እንኳ አያምኑም» አለው።

- አብርሃም ለሀብታሙ ሰው ምን አለው?

- አብርሃም የሀብታሙ ሰው ወንድሞች የእግዚአብሔርን ቃል መስማት ካልፈልጉ አንድ ሰው ከሙታን ተነስቶ ቢሄድም አያምኑም አለው።

- እኛ የእግዚአብሔርን ቃል የማንሰማና የማናምን ከሆነ ሊያድነን የሚችል ሌላ ነገር ይኖራልን?

-የለም።